# በሕይወት ባሉ ዘመዳሞች መካከል ስለሚደርግ የአካል ክፍሎች ንቅለ ተከላ ህክምና አሰጣጥ መመሪያ

ጥር 2007 ዓ.ም

# በሕይወት ባሉ ዘመዳሞች መካከል ስለሚደርግ የአካል ክፍሎች ንቅለ ተከላ ህክምና አሰጣጥ መመሪያ

## መግቢያ

ከበርካታ አመታት በፊት በበለፀጉት ሀገሮች የተጀመረው የንቅለ ተከላ ህክምና  በሃገራችን ከአይን ብሌን ንቅለ ተከላ በስተቀር ሳይተገበር የቆየ ቢሆንም በአካል ክፍሎች ህመም ምክንያት ለሚሰቃዩ እና ለሞት ለሚዳረጉ ግለሰቦች የህክምና መፍትሄ ከመስጠት አንፃር ህክምናው እንዲዳብርና በስፋት እንዲሰጥ ለማድረግ የአሰራር መመሪያ በማፈለጉ፤

በሃገራችን የህግ ስርዓት ንቅለ ተከላ  የሚካሄደው ለንግድ አላማ ካልሆነ እና የለጋሹን ጤንነት ሁኔታ ማይጎዳ መልኩ እስከተካሄደ ድረስ ንቅለ ተከላ ማካሄድ እንደሚቻል የተደነገገ በመሆኑ፤

ምንም እንኳን ህክምናው የጤና አገልግሎት አካል መሆኑ በሃገራችን የተለያዩ ህጎች ተደንግጎ የሚገኝ እና ህጎቹም አገልግሎቱን ለመስጠት በቂ ናቸው ሊባል ቢችልም በንቅለ ተከላ ህክምና ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ ሌሎች ጉዳዮችን ከሃገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም በህግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሃገራችን በአሁኑ ጊዜ ንቅለ ተከላ ለማካሄድ የሚችሉ የጤና ተቋማትን መፍጠር እንደሚቻል ከግንዛቤ በማስገባት ህክምናውን  በነዚሁ የጤና ተቋማት በመስጠት ዜጎች ህክምናውን ለማግኘት ወደ ሌላ ሃገር በመሄድ የሚያወጡትን ከፍተኛ ወጪ እንዲያስቀር እንዲሁም ህክምናውን ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለሁሉም ታማሚዎች ተደራሽ እንዲሆን ወጥ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋት፤

ከሌሎች ሃገራት ተሞክሮ የንቅለ ተከላ ህክምና አገልግሎት ለንግድ አላማ መዋሉን ለመቆጣጠር አዳጋች ሆኖ ለከፍተኛ የማህበራዊ ቀውስና የወንጀል ድርጊት የሚያጋልጥ መሆኑን በመረዳት የሰዎች የአካል ክፍሎች ለመነገጃና ለማትረፊያ እንዳይሆኑ ለመከላከል፤

ከንቅለ ተከላ ህክምና ጋር ተያይዞ ሊከሰቱ የሚችሉ የሰዎችን ሰብአዊ ክብርና መሰረታዊ ነፃነቶች የሚጋፉ ማናቸውም ከስነምግባር ውጪ የሆኑ ህገወጥ አሰራሮችን ለመከላከል፤

በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ተግባራዊ የሚደረገው የንቅለ ተከላ ህክምና የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ባላቸው ግለሰቦች መካከል ብቻ መሆኑን ለመደንገግ፤

በንቅለ ተከላ ህክምና ተሳታፊ የሚሆኑ አካላትን ከመደበኛ ተግባርና ሃላፊነታቸው በተጨማሪ ህክምና ውስጥ ተሳታፊ በመሆናቸው የሚጠበቅባቸውን ተግባርና ሃላፊነት በዝርዝር ለማስቀመጥ፤

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 በአንቀፅ 10 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. <u>**አጭር ርዕስ**</u>

ይህ መመሪያ "በህይወት ባሉ ዘመዳሞች መካከል ስለሚደረግ የአካል ክፍሎች ንቅለ ተከላ ህክምና አሰጣጥ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>**አውጪው አካል**</u>

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 10 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

3. <u>**ትርጉም፡-**</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1. “ንቅለ ተከላ” ማለት ከአንድ ሰው የአካል ክፍል ወስዶ ወደ ሌላ ሰው አካል መትከል ማለት ነው፡፡
2. “አካል ልገሳ” ማለት አካልን በፈቃደኝነት ለሌላ ሰው አሳልፎ ለንቅለ ተከላ አላማ መስጠት ማለት ነው፡፡
3. “ለጋሽ” ማለት ከተለጋሽ ጋር የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና ያለው ሆኖ አካሉን ለተቀባይ በፍቃደኝነት የሚሰጥ ሰው ማለት ነው፡፡
4. “ተቀባይ” ማለት ከለጋሽ ጋር የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና ያለው ሆኖ የለምንም ክፍያ ከለጋሽ አካል የተሰጠው ሰው ነው፡፡
5. “አካል” ማለት በዚህ መመሪያ ተፈቀዱ አካላትን ወይም የአካል ክፍሎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡
6. “ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር” ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡
7. “የጤና ተቋም” ማለት የጤና ማበልፀግ፣ የበሽታ ከላከል፣ ማከምና መልሶ ማቋቋም ስራዎችን ወይም አገልግሎት የሚያከናውን የመንግስት፣ መንግስታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ነው፡፡
8. “የህክምና ባለሙያ” ማለት ህመምተኛውን በመመርመር የበሽታውን አይነት የሚለይና በመድሃኒት ወይም አካልን በመቅደድ የሚያክም የሰው ሃኪም ወይም እነዚህኑ ተግባራት እንዲያከናውን በባለስልጣኑ የተፈቀደለት የጤና ባለሙያ ነው፡፡
9. “ባለስልጣን” ማለት የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒት እና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

10. “የብሄራዊ የንቅለ ተከላ ኮሚቴ” ማለት ከልገሳ በፊት የለጋሹን ፍቃደኝነት የሚያረጋጥ እና በለጋሽ እና በተለጋሽ መካከል የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና መኖሩን በማረጋገጥ ንቅለ ተከላውን ለሚያከናውነው ተቋም አካል ልገሳ እንዲከናወን ፍቃድ የሚሰጥ በባለ ስልጣኑ የሚቋቋም ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት የተውጣጡ አባላት ሰስብስብ ነው፡፡

11. “የንቅለ ተከላ ተቋም” ማለት በባለ ስልጣኑ ልዩ ፍቃድ የተሰጠው የንቅለ ተከላ ተግባር የሚያከናውን የጤና ተቋም ነው፡፡

12. “በምክር ላይ የተመሰረተ ፍቃድ” ማለት ንቅለ ተከላ የማድረግ ሂደቱ፣ ተፅዕኖ ፣ ጉዳቱና ጠቀሜታውን ለጋሹ በሚረዳው ቋንቋ ወይም ምልክት ምክር ተሰጥቶት ፍቃዱን መስጠት ነው፡፡

13. “የህክምና ደረጃ” ማለት ባለስልጣኑ ለጤና ተቋም ፍቃድ ሲሰጥ የጤና ተቋማቱ ማሟላት ያለባቸው መስፈርት ሲሆን መስፈርቱ በህግና የሙያው ስነምግባር የሚጠይቀውን ሁኔታዎች መሰረት ያደረገ ነው፡፡

14. “ዘመዳሞች” ማለት በለጋሽና በተለጋሽ መካከል የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያላቸው የተፈጥሮ ሰዎች ናቸው፡፡

በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል ፡፡

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

1. ይህ መመሪያ በህይወት ባሉ የጋብቻ እና የስጋ ዘመዳሞች መካከል የሚደረግ የአካል ልገሳን እና የንቅለ ተከላ ህክምናን በተመለከተ የሚካሄዱ ተግባሮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. መመሪያው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ላይ ተፈፃነት የለውም፤

ሀ. አእምሮው ከሞተ ሰው የሚደረግ ንቅለ ተከላ፣

ለ. ከሞተ ሰው የሚደረግ የአካል ንቅለ ተከላ፣

ሐ. የመራቢያ አካላት ንቅለ ተከላ፣

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ለጋሽ እና በምክር ላይ የተመሰረተ ፍቃድ</u>

### 5. <u>ለጋሽ ስለመሆን</u>

የሰው የአካል ክፍል በህይወት ካለ ለጋሽ ለንቅለተከላ  አላማ የሚወሰደው በለጋሽና በተለጋሽ መካከል የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና ሲኖር እና በምክር እና ገለፃ ላይ የተመሰረተ ፍቃድ ከለጋሹ ሲገኝ ብቻ ነው።

### 6. <u>በህግ ስለሚፀና ፍቃድ</u>

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 5 መሰረት በምክር ላይ የተመሰረተ ፍቃድ እንደተሰጠ የሚቆጠረው ፡-

   ሀ. ለጋሹ ልገሳውን ለማድረግ በህግ የሚፀና ፍቃድ መስጠት የሚችም ሲሆን፣

   ለ. ለጋሹ ፍቃዱን የሰጠው በሙሉ ፍቃደኝነት ወይም ባለመታለል ወይም ከተፅዕኖ ውጪ ወይም ሳይገደድ ወይም በማንኛውም መንገድ ጉድለት በሌለበት ሁኔታ ሲሆን፣

   ሐ. ለጋሹ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 7 መሰረት በቂ መረጃ ሲያገኝ፣

   መ. ለጋሹ መስማማቱን የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ ሲኖር ይሆናል።

2. በዚህ አንቀፅ (1) (ሀ) መሰረት ህግ የሚፀና ፍቃድ መስጠበት የሚችል ማለት

   ሀ. እድሜው 18 እና ከዚያ በላይ የሆነ

   ለ. የአእምሮ ጤና እክል የሌለበት  ማት ነው።

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለጋሹ እድሜው 18 አመት ባይሞላውም በልዩ ሁኔታ በሞግዚቱ ወይም ባሳዳሪው ፍቃድ ሰጪነት የፍልቂ አጥንት(ቦን ማሮው) ሊለግስ ይችላል፡፡

4. የለጋሹ ፍቃድ የተገኘው በማታለል ወይም በማስገደድ ወይም በማስፈራራት ወይም የገንዘብ ጥቅም ለማስገኘት ወይም ለማግኘት ወይም በማንኛውም መንገድ ፍቃድን በህግ ፊት እንዳይፀና በሚያደርጉ በህግ በተደነገጉ ሁኔታ የተገኘ ከሆነ ፍቃዱ ጉድለት እንዳለበት ተቆጥሮ ውድቅ ይሆናል፡፡

5. ለጋሹ በማንኛውም ጊዜ ከላይ በተዘረዘረው አግባብ የሰጠውን ፍቃድ መሰረዙን ንቅለተከላው ከመከናወኑ በፊት በፅሁፍ ወይንም በቃል ወይም በማንኛውም ሁኔታ ሊገልጽ ይችላል፡፡

7. **<u>ምክር እና ገለፃ</u>**

1. በዚህ መመሪያ መሰረት የለጋሹ ፍቃድ በምክር እና ገለፃ ላይ የተመሰረተ እንደሆነ የሚቆጠረው፣

ሀ. ለጋሹ በማንኛውም ሰዓት የልገሳውን ፍቃድ መሰረዝ እንደሚችል ሲገለፅለት፤

ለ. ለጋሹን ለንቅለተከላ ለማዘጋጀት በሰውነት ላይ የሚደረግ የህክምና ሂደት፣ የሚወሰድ መድሃኒት እና መድሃኒቱ በሰውነት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ሲገለፅለት፤

ሐ. ልገሳው እንዴት እንደሚከናን እና ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ሲገለፅለት

መ. ልገሳው በአጭር እና በረጅም ጊዜ ሊያስከት የሚችለው የጎንዮሽ ጉዳት ካለ ሲገለፅለት፤

ሠ. ከልገሳው በኃላ ሊመጡ የሚችሉ የአኗኗር ለውጦች እና መወሰድ ስለሚገባው ጥንቃቄ እና

ረ. ሌሎች አግባብ የሆኑ የህክምና እና ማህበራዊ ሁኔታዎች ገለፃዎች ሲደረግለት ነው፡፡

2. ማንኛውም ምክር እና ገለፃ ለጋሹ በሚረዳው ቋንቋ ወይም ምልክት መደረግ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተዘረዘሩት ለለጋሹ የሚደረጉ ምክር እና ገለፃዎች ከልገሳው በፊት መሰጠታቸውን የሚያመላክት ሠነድ በተቋሙ ተዘጋጅቶ እና ተረጋግጦ ለኮሚቴው መቅረብ አለበት፡፡

# ክፍል ሶስት

## ስለ ለጋሽ መረጃ እና የመረጃ ጥንቅር

8. ***መረጃ ስለ መመዝገብ***

1. ይህን መመሪያ መሰረት በማድረግ በሚዘጋጅ የአሰራር ፕሮቶኮል ኮሚቴው የለጋሽ እና የተለጋሹን ሙሉ መረጃ ይመዘግባል፡፡

2. ስለለጋሹ የተሰጠው መረጃ በተገቢው ሁኔታ ሰነድ ተደርጎ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

3. የህክምና ተቋማት የአካል ንቅለተከላ ያደረጉ ሰዎችን ያጋጠሟቸውን የጎንዮሽ ጉዳት ወይም ማንኛውም ውጤት መዝግበው ማስቀመጥ ይገባቸዋል፡፡

4. የተመዘገቡትን መረጃዎች በየጊዜው ለባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ሚስጥራዊነትን በጠበቀ መልኩ ማሳወቅ ይገባቸዋል፡፡

5. የአካል ንቅለተከላን ደህንነት እና ጥራት ለማረጋገጥ በአካል ንቅለተከላ ላይ የተሰማራው የህክምና ቡድን አስፈላጊ የሆኑ የለጋሽ መረጃዎችን የመሰብሰብ እና በለጋሹ ላይ ያለውን ውጤት ለለጋሹ በአግባቡ መግለፅ አለበት፡፡

9. **ስለመረጃ ይዘት**

1. በአካል ንቅለተከላ ላይ የተሰማራ የህክምና ባለሙያ ከንቅለተከላ በፊት ንቅለተከላው የሚካሄድበትን ተቋም፣ የአካል እና የለጋሽ መለያ ፣ የለጋሹ የደም አይነት ፣ ፆታ፣ የትውልድ ቀን እና ዓመተ ምህረት፣ ክብደት፣ ቁመት፣ የአደንዛዥ እፅ ተጠቃሚነት፣ ተላላፊ በሽታዎችን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ መሰረታዊ የግል መረጃዎችን በመሰብሰብ የአካልና ለጋሽ መለያ መረጃዎችን መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

2. እንደ መረጃው መገኘት እና አስፈላጊነት የላብራቶሪ መረጃችን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን መሰብሰብ አለባቸው፡፡

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተጠቀሱት እንጉዳዩ አግባብነት ለተለጋም ያገለግላሉ፡፡

## 10. <u>መረጃን ስለማግኘት</u>

1. የለጋሽን እና የተለጋሽን የወደፊት ጤንነት በአግባቡ ለመጠበቅ ሲባል የአካል ንቅለተከላ የሚያካሄድ ተቋምና ባለሙያ የለጋሽ እና የተለጋሽን የጤና እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን ወደኃላ ተመልሶ ለማግኘት እንዲቻል መረጃ መያዝ አለባቸው፡፡

2. ንቅለተከላ የሚካሄድበት ተቋም ለጋሽ እና ተለጋሽን ወደኃላ ተመልሶ ለማግኘት እንዲቻል ለጋሽ እና ተለጋሽ የሚለዩበትን እና የሚገኙበትን ስርዓት የመዘርጋት ሃላፊነት አለበት፡፡በንቅለተከላ ህክምና ምክንያት የሚገኝ ማንኛውም የህክምና መረጃ ምስጢራዊ በሆነ መንገድ መቀመጥ እና ህግ በማይፈቅደው ሁኔታ መጋለጥ የለበትም፡፡

3. ባለስልጣኑ ወይም በንቅለተከላ ጊዜ የሚሳተፍ ማንኛውም አካል መረጃን ወደኃላ ተመልሶ ማግኘት እንዲቻል በሂደት የተገኘን መረጃ በአግባቡ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

4. መረጃን ወደኃላ ተመልሶ ማግኘት እንዲቻል በዚህ መመሪያ መሰረት የተሰበሰበ መረጃ እስከ ለ30 (ሰላሳ) አመታት መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት

## የአካል ክፍሎች ንቅለ ተከላ

### 11. የአካል ክፍሎች ጥበቃ፣ ክብር እና ደህንነት

1. ማንኛውም የአካል ክፍል እና ህብረ ህዋስ ለተቀባዩ ሊሰጥ የሚችለው ደህንነቱ፣ ጥራቱ እና ተስማሚነቱ ሲረጋገጥ ነው፤

2. የአካል ክፍሎች ደህንነት እና ጥራትን በተመለከተ ባለስልጣኑ የአሰራር መስፈርት ሊያወጣ ይችላል፤

3. የአካል ክፍሎች እና ህብረ ህዋስ ህክምና በመስጠት ላይ የሚሳተፍ ባለሙያ እና ተቋም የአካሉን ጥራት እና ደህንነት ለማስጠበቅ ተገቢውን ደረጃ እና መስፈርት መከተል አለበት፡፡

4. አካል ክፍል ለጋሽ የሚመረጠው ይህን መመሪያ መሰረት በማድረግ የሚዘጋጅ ዝርዝር ፕሮቶኮል ፣ የጤንነት ሁኔታውን እና የህክምና ታሪኩን መሰረት በማድረግ መሆን ይኖርበታል፡፡ በዚህ አይነት ምዘና ንቅለ ተከላው በጤንነታቸው ላይ ጉዳት የሚያደርስባቸውን ሰዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ መፈቀድ የለበትም፡፡

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 4 እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠቀሰው የጤንነት ጉዳት ንቅለተከላውን ለማድረግ የሚያስችል መሆን አለመሆኑን የአገልግሎት ሰጭ ተቋሙ የህክምና ቦርድ የሚወሰነው ይሆናል፡፡

6. የለጋሹን የአካል ጉዳትና የስነልቦና ተፅእኖ ለመቀነስ የአካል ክፍል ከመወሰዱ በፊት አግበብ ያለው የህክምና ምርመራና እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

### 12. ከንቅለተከላ በኃላ የሚደረግ እንክብካቤ

ሀ. ከንቅለተከላው በኃላ ለለጋሽም ሆነ ለተቀባይ የሚደረገው አግባብ ያለው የህክምና እንክብካቤ ንቅለተከላውን የሰራው ተቋም ማከናወን አለበት፡፡

ለ. የህክምና ቅብብሎሽ ስርዓቱ በሚፈቅደው መሰረት የድህረ እቅለተከላ ህክምና በሌላ ተቋም ሊደረግ ይችላል፡፡

ሐ. ንቅለተከላ ከመከናወኑ አስቀድሞ ለህክምና የሚያስፈልገው አጠቃላይ ወጪ በህክምና ተቋሙ ተሰልቶ ለተለጋሽ መገለፅ አለበት፡፡

# ክፍል አምስት

# ተግባርና ሃላፊነት

## 13. የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተግባርና ሃላፊነት

ሀ. ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ የብሄራዊ የንቅለተከላ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፤

ለ. የኮሚቴውን ስራ በየጊዜው ይቆጣጠራል፣ ሪፖርቶችን ይገመግማል፣ በሚቀርብለት ሪፖርት መሰረት ማስተካከያ ይሰጣል፤

ሐ. ኮሚቴው ለስራው የሚያስፈልጉትን ማንኛውም ግብአቶች ከባለስልጣኑ ጋር በጋራ በመሆን እንዲሟሉለት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 14. የባለስልጣኑ ተግባርና ሃላፊነት

ሀ. የአካል ንቅለተከላ ለሚያካሄዱ የጤና ተቀዋማት እና ባለሙያዎች ልዩ ፍቃድ ይሰጣል፤

ለ. የአካል ንቅለተከላ ለሚያካሄዱ የጤና ተቋማት መሟላት የሚገባቸውን መስፈርት ያወጣል፤

ሐ. የአካል ንቅለተከላ ለማካሄድ ፍቃድ የተሰጣቸውን የጤና ተቋማት ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣ በየአመቱ ፍቃድ ያድሳል፣ ከደረጃቸው ዝቅ ያሉትን ፍቃዳቸውን ያሰርዛል፤

መ. የአካል ንቅለተከላ የሚያካሄዱ የጤና ተቋማት የሚያገኛቸውን መረጃዎች በሚስጥር ይጠብቃል፤

ሠ. የአካል ንቅለተከላ የሚያካሄዱ የጤና ተቋማት ሪፖርት በየጊዜው እየተከታተለ ይቀበላል፤ በሪፖርቱ ላይ ግብረ መልስ እና የስራ ማስተካከያ ትዕዛዝ ይሰጣል፤

ረ. በዚህ መመሪያ መሰረት የሚቋቋመውን ኮሚቴ ለስራው የሚያስፈልጉትን ማንኛውም ግብአቶች ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በጋራ በመሆን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 15. የጤና ተቋም ተግባርና ሃላፊነት

በዚህ መመሪያ መሰረት የንቅለተከላ የሚያከናውን ማንኛውም የጤና ተቋም ፡-

ሀ. የአካል ንቅለተከላ ለማካሄድ የሚችለው ከባለስልጣኑ ልዩ ፍቃድ ሲሰጠው ብቻ ነው፤

ለ. ፍቃድ ባገኘበት መስፈርት መሰረት ስራን ያከናውናል፣ፍቃዱን በየአመቱ ያድሳል፣ፍቃዱን ለሌላ ሶስተኛ ወገን ወይም ተቋም ማስተላለፍ አይችልም፤

ሐ. የንቅለተከላን አስፈላጊነት በተቋሙ የህክምና ቦርድ ያስወስናል፤

መ. ባለስልጣኑ በወሰነው የጊዜ ገደብ ሪፖርት ያደርጋል፣ በሪፖርቱ መሰረት የተሰጡትን ግብረመልሶች እና ማተካከያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤ባለስልጣኑ የጠየቀውን ማናቸውንም መረጃ ይሰጣል፤

ሠ. የለጋሽን በምክር ላይ የተመሰረተ ፍቃድ እና የዝምድና መረጃዎችን አደራጅቶ ለንቅለተከላ ኮሚቴው ያቀርባል፤

ረ. የለጋሽንና የተለጋሽን መረጃ በሚስጥር ይጠብቃል፤የጤንነትን ሁኔታ በአግባቡ ይመረምራል፤ ከልገሳ በኃላ ወይም በልገሳው ጊዜ በጤና ላይ ሊደርስ የሚችል መታወክ አለመኖሩ በምርመራ ያረጋግጣል፤

ሰ. ከኮሚቴው ፍቃድ ሲያገኝ ለንቅለተከላ የሚረዳ ቅድመ ምርመራ እና ህክምና ያካሄዳል፤

ሸ. ለንቅለተከላ ለሚወሰደው የለጋሹ አካል ከተለጋሹ ጋር የሚስማማ መሆኑን ያረጋግጣል፤

በ. ንቅለተከላ ከመካሄዱ በፊት ለጋሹ በማንኛውም ሰዓት ፍቃደኝነቱን የማንሳት መብቱን ያከብራል፤

ቀ. ለጋሹ ለንቅለተከላ ፍቃደኛ እንዲሆን ወይም ፍቃደኝነቱን እንዲያነሳ ለማድረግ የማባበል፣ የማታለል፣ የማሳመን ስራዎች እንዳይሰሩ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፤

ተ. ንቅለተከላውን የሚያካሄደው ተቋም በዚህ መመሪያ መሰረት ከንቅለ ተከላ በፊት የአካል እና ለጋሽ መለያ ስራ መደረጉን፣በዚሁ መሰረት መረጃ መያዙን እና አካሉ ከወጣ በኃላ በአግባቡ ለመጠበቅ ቅድመ ሁኔታዎች እንደተሟሉ ማረጋገጥ አለበት፣

ቸ. ለአካል ንቅለተከላ የሚውሉ ማንኛውም የህክምና መሳሪያዎች እና ተያያዥ መገልገያዎች አግባብ ያለውን የደህንነት እና ጥራት ደረጃ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት።

ኘ. ለንቅለተከላው አስፈላጊ የሆኑ የህክምና ዝርዝር ፕሮቶኮል ያወጣል።

16. <u>የጤና ባለሙያዎች ሃላፊነት</u>

ሀ. የአካል ለጋሽ መረጣ ወይም ምዘናን ጨምሮ አካል በሚሰጥበት እና ጥበቃ በሚካሄድበት ተቋም የሚካሄድ ማንኛውም የህልምና ተግባር መካሄድ ያለበት አግባብ ባለው እና በባለስልጣኑ የተፈቀደለት የህክምና ባለሙያ ብቻ ነው፡፡ በማንኛውም አካል ንቅለተከላ እስከ አካል ማስወገድ ድረስ የሚሳተፍ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ብቃት ያለው እና ተፈላጊውን ስልጠና ያገኘ መሆን አለበት፡፡

ለ. የጤና ባለሙያ የአካል ልገሳው በጤናቸው ላይ ጉዳት የሚያደርስባቸው ሰዎች ለልገሳ ተሳታፊ እንዲሆኑ መፍቀድ የለበትም፡፡

ሐ. የአካል ንቅለተከላ ውስጥ የሚሳተፍ ማንኛውም የህክምና ባለሙያ ወይም የጤና ተቋም የአካሉን ጥራት እና ደህንነት ለማስጠበቅ ተገቢውን መስፈርትና ፕሮቶኮል መከተል አለበት፡፡

## 17. የብሄራዊ አካል ንቅለተከላ ኮሚቴ ተግባር፣ኃላፊነትና አሰራር

በዚህ መመሪያ መሰረት የንቅለተከላ ከመካሄዱ በፊት የለጋሹን ፍቃደኝነት እንዲሁም በለጋሽና በተለጋሽ መካከል የጋብቻ ወይም የስጋ ዝምድና መኖሩን የሚያረጋግጥ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ የሆነ ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን ኮሚቴው፡-

1. ለንቅለተከላ ህክምና የቀረቡትን ለጋሽ እና ተለጋሽ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 8 በተሰጠው ዝርዝር መሰረት ዝምድና ያጣራል፤
2. የለጋሽን ፍቃደኝነት እና ከተለጋሹ ጋር ከአካል ንቅለተከላው ጋር የተያያዘ የጥቅምና የንግድ ግንኙነት እንደሌለው ያረጋግጣል፤
3. ለጋሽ እና ተለጋሹ ስልጣን ካለው አካል የሚያቀርቡትን መረጃዎችን ይመረምራል፤
4. ኮሚቴው 8 (ስምንት) ያህል አባላት ይኖሩታል፡፡

   ሀ. የፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ተወካይ. ሰብሳቢ

   ለ. በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሜዲካል አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ……………ፀሃፊ

   ሐ. በፌዴራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የህግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት…አባል

   መ. የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚነስቴር ተወካይ…..አባል

   ሠ. የሴቶችና ህፃናት ሚኒስቴር ተወካይ………አባል

   ረ. የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ተወካይ…….አባል

   ሰ. የኢትዩጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ተወካይ….አባል

   ሸ. የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ተወካይ…..አባል

ቀ. የሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ተወካይ…አባል

በ. የኢትዮጵያ የእምነት ተቋማት ህብረት ተወካይ…አባል

5. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ኮሚቴው ስብሰባውን ያካሂዳል፤
6. የኮሚቴው ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ሲሆን እኩል ድምፅ ሲገኝ የኮሚቴው ሰብሳቢው ያለበት ወገን አሸናፊ ይሆናል፤
7. የኮሚቴው መሰብሰቢያ ጊዜ እና ቦታ በኮሚቴው ዝርዝር የአሰራር ቢጋር ይወሰናል፤
8. ኮሚቴው ዝርዝር የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ለሚኒስት አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 18. የተከለከሉ ተግባራት

ይህን መመሪያ መሰረት በማድረግ፡-

ሀ. በእርግዝና ወቅት ካለች ሴት የአካል ክፍል መውሰድ፣

ለ. በእስር ላይ ካሉ ሰዎች የአካል ክፍል መውሰድ፣

ከአእምሮ ህሙማን የአካል ክፍል መውሰድ አይቻልም፡፡

### 19. የህግ ተጠያቂነት

1. ማንኛውም ንቅለተከላ የሚያከናውን የህክምና ባለሙያ እና ተቋም ንቅለተከላ ሲያከናውን የሙያውን የስለምግባር ደንብ እና አግባብ ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች ማክበር አለበት፡፡
2. በዚህ መመሪያ የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች በተቃረነ መልኩ ንቅለተከላ የሚያካሄድ የህክምና ባለሙያ ወይም ተቋም የወንጀልና የፍትሐብሔር ተጠያቂነቱ እንደተጠበቁ ሆነው

   ሀ. ባለስልጣኑ እንደነገሩ ሁኔታና እንደ ጉዳዩ ክብደት ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ፍቃድ ስረዛ ሊደርስ የሚችል እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

   ለ. ተጎጂው አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ በማድረግ ካሳ ሊያስከፍል ይችላል፡፡

   ሐ. የካሳ አከፋፈልን በተመለከተአግባብ የሆነ የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### 20. የመተባበር ግዴታ

ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን የሚመለከታቸው አካላትና የጤና ተቋማት የመተግበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 21. የቅሬታ አቀራረብ

ሀ. ከሙያ ስለምግባር ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች ለባለስልጣኑ መቅረብ አለባቸው፡፡

ለ. በብሄራዊ አካል ንቅለተከላ ኮሚቴ አሰራርና ውሳኔዎች ዙሪያ ያሉ ቅሬታዎች ለሚነስቴሩ መቅረብ ይችላሉ፡፡

## 22. መመሪያውን ስለሚሻሻልበት ሁኔታ

ሚኒስቴሩ መመሪያውን ተግባራዊ ሲያደርግ ክፍተቶች ሲያጋጥሙ መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 23. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያና ልማዳዊ አሰራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 24. መመሪያው ተፈፃሚ ስለሚሆንበት

ይህ መመሪያ ከጥር ……ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ከሰተብርሃን አድማሱ(ዶ/ር)

የጤና ጥበቃ ሚኒስትር